ቅጽ 2 ጥር/2014 ዓ.ም

የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት

# ፓርላማ ዜና መጽሔት

6ኛው የኢፌዴሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በ1ኛ ዓመት የስራ ዘመኑ በጥር ወር 4ኛ መደበኛ እና 3ኛ ልዩ ስብሰባዎችን አካሂዷል። ምክር ቤቱ የጤና ሚኒስቴርን እና የፍትህ ሚኒስቴርን የ2014 በጀት ዓመት የ6 ወራት የእቅድ አፈጻጸም ሪፖርት አድምጧል። አገራዊ የምክክር ኮሚሽኑን የሚመሩ ዕጩ ኮሚሽነሮችን በመምረጥ ሂደት የተለያዩ አካላት የተሳተፉበት በ42 ዕጩ ኮሚሽነሮች ላይ የአስተያየት መስጫ መድረክ ተካሂዷል። የ6ኛው ምክር ቤት የፓርላማ ሴት ተመራጭ ኮከስ የምስረታ ጉባኤውን ያካሄደው በዚሁ ወረ ነው። የጥር ወር የፓርላማ ዜና መጽሄታችን እነዚህን አበይት ምክርቤታዊ ጉዳዮች የያዘ መረጃ ይዛ ወጥታለች።

መልካም ንባብ!

## ርዕሶች

- የ2014 በጀት ዓመት ተጨማሪ በጀትና ወጪ አሸፋፈን ማስተካከያ 122 ቢሊየን ብር
- አገረዊ ምክክር ኮሚሽን ዕጩ ኮሚሽነሮች
- የፍትሕ ሚኒስቴር የ2014ዓ.ም የ6ወራት የዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት
- የጤና ሚኒስቴር የ2014ዓ.ም የ6 ወራት እቅድ አፈጻጸም ሪፖርት
- የፓርላማ ተመራጭ ሴቶች ኮከስ ምስረታ

# ምክር ቤቱ የ2014 በጀት ዓመት ተጨማሪ በጀትና ወጪ አሸፋፈን ማስተካከያ 122 ቢሊየን ብር አጸደቀ፤



ምክር ቤቱ ጥር 20 ቀን 2014 ዓ.ም ባካሄደው 3ኛ ልዩ ስብሰባ ከተያዙ አጀንዳዎች አንዱ የሆነው የፌዴራል መንግስት የ2014 በጀት ዓመት ተጨማሪ በጀትና ወጪ አሸፋፈን ማስተካከያ ረቂቅ አዋጅ፤ አዋጅ ቁጥር 1266/2014 ሆኖ በ9 ተቃውሞ በ7 ድምጸ ተዓቅቦ በአብላጫ ድምጽ አጽድቆታል።



በአገራችን በተከሰተው ጦርነት ምክንያት ተጨማሪ በጀት በማስፈለጉና ከኢኮኖሚ እንቅስቃሴ አኳያ የሚሰበሰበው ገቢ በወቅቱ ያለውን ክፍያ ጥያቄ ለማስተናገድ አስቸጋሪ ሁኔታ በመፈጠሩ እንዲሁም ወቅቱ የፈጠረውን ተጨማሪ የወጪ ፍላጎት በበጀት ሽግሽግ ለማስተናገድ ስላልተቻለ ተጨማሪ የበጀት ጥያቄና የወጪ አሸፋፈን ተግባራዊ ማድረግ አስፈላጊ እንደሆነ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የመንግስት ተጠሪ ሚኒስትር የተከበሩ አቶ ተስፋዬ በልጂጌ ገልጸዋል።



በመሆኑም በጀቱ ለመከላከያ 90.0 ቢሊየን ብር፣ ለዕለት ዕርዳታ 8.0 ቢሊየን ብር፣ ለመጠባበቂያ 8.0 ቢሊየን ብር፣ ለካፒታል ፕሮጀክት 7.0 ቢሊየን ብር፣ ለወጪ አሸፋፈን ማስተካከያ 9.0 ቢሊየን ብር በአጠቃላይ 122.0 ቢሊየን ብር ሆኖ እንዲጸድቅ የውሳኔ ሃሳብ ቀርቧል።

የኮቪድ 19 ወረርሽኝ ካለበት ሁኔታ አንጻር በኢኮኖሚው ላይ ጫና ይፈጥራል ወይ? ለመከላከያ የተመደበው በጀት መከላከያ ለሃገር እየከፈለ ካለው ዋጋ አንጻር ቢያንስ እንጂ አይበዛበትም፤ በድርቅ ለተጎዱ አካባቢዎች በጀት ያልተያዘበት ምክንያት ቢገለጽ፤ በጦርነቱ ምክንያት በአማራና በአፋር ክልሎች ከ ቤ ት ን ብ ረ ታ ቸ ው

የተፈናቀሉ ዜጎችና የወደሙ ተቋማትን መልሶ ለመገንባት የተመደበው በጀት ከውድመቱ ስፋት አንጻር በተመደበው በጀት ስራውን መስራት ይቻላል ወይ? በብድር መሸፈኑ በመንግስት የዕዳ ጫና ላይ የሚኖረው ተጽዕኖ ታይቷል ወይ? የሚሉ ጥያቄዎችና አስተያየቶች በምክር ቤት አባላት ተነስተዋል፡፡

የገንዘብ ሚኒስቴር ሚኒስትር ዴኤታ እዮብ ተካልኝ (ዶ/ር) ኮቪድ 19 በኢኮኖሚው ላይ የሚያመጣውን ተጽዕኖ በየጊዜው በመገምገም ተጽዕኖውን የተቋቋመ ኢኮኖሚ መገንባት እንደተቻለ፣ በህወሐት ወረራ ምክንያት የወደሙ ተቋማትን ለመገንባት ከችግሩ አንገብጋቢነት አንጻር የጤና ሚኒስቴር፣ የትምህርት ሚኒስቴር፣ የገንዘብ ሚኒስቴር እንዲሁም ሌሎች የመንግስት የልማት ደርጅቶች ተቀናጅተው በርካታ የመልሶ ማቋቋም ስራዎችን በመስራታቸው የጤና ተቋማት በፍጥነት ወደ ስራ የገቡበት ሁኔታ እንዳለ ገልጸዋል፡፡

አካለውም ከባድ ጉዳት የደረሰባቸውን የትምህርት ተቋማት ግንባታ ለማስጀመር ትምህርት ሚኒስቴር እና ከገንዘብ ሚኒስቴር ከዲያስፖራው ማህበረሰብና ከተለያዩ ዓለም አቀፍ ግብረ ሰናይ ድርጅቶች ጋር በመቀናጀት ግንባታዎች ባጠረ ጊዜ ተገንብተው ለህብረተሰቡ አገልግሎት መስጠት የሚችሉበት ሁኔታ ለማመቻቸት የገቢ ማሰባሰብ ስራው ተጠናክሮ የቀጠለበት ሁኔታ እንዳለ ገልጸው የተመደበው 5 ቢሊየን ብር የመልሶ ግንባታ ፕሮጀክቶችን ለማስጀመር የተመደበ በጀት እንደሆነ አብራርተዋል፡፡

በተያያዘም በድርቅ ጉዳት ለደረሰባቸው አካባቢዎች የአደጋ ስጋት መከላከል በሚመራበት የአሰራር ማዕቀፍ እንደሚስተናገድ የገለጹት እዮብ ተካልኝ (ዶ/ር) አጠቃላይ ወጪው በኢኮኖሚው ላይ የሚያሳድረው ተጽእኖ ካለው አገራዊ ሁኔታ አንጻር ችግሩ እንዳይባባስ በጥብቅ የማክሮ ኢኮኖሚ ዲስፕሊን ሲመራ እንደቆየ ጠቀመው በቀጣይም ተጠናክሮ እንደሚቀጥል አብራርተዋል፡፡

> “አገራችን ከገጠማት ቀውስ አንጻር የተፈራውን ያህል ግሸበት ያልታየው ኢኮኖሚው በጠንካራ ማክሮ ኢኮኖሚ ዲሲፕሊን ስለሚመራ ነው፡፡”

በዚሁ እለት ተሰይሞ የዋለው ምክር ቤት የማህበረሰብ አቀፍ የጤና መድህን ረቂቅ አዋጅን ለማሻሻል የወጣውን ረቂቅ አዋጅ ከምክር ቤት አባላት የተነሱ አስተያየቶችና ጥያቄዎችን ጨምሮ ለዝርዝር እይታ ለጤና፣ ማህበራዊ ልማት፣ ባህልና ስፖርት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ መርቶታል፡፡

# በአሸባሪው የህወሐት ቡድን የጥፋት ሴራ ውስጥ እጃቸው አለበት ተብለው የተጠረጠሩ ግለሰቦች የተፈቱበት ምክንያት ላይ ማብራሪያ ተሰጠ፤



በ6ኛው የኢፌዴሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት 1ኛ ዓመት የስራ ዘመን ጥር 26 ቀን 2014 ዓ.ም ባካሄደው 4 ኛ መደበኛ ስብሳባ የፍትሕ ሚኒስቴር የ6ወር የዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት ቀርቧል።

በሪፖርቱም የምርመራ መዝገቦችን ከማጣራት አንጻር፣ ክክርክር መዛግብት አንጻር በተደራጀ፣ በኢኮኖሚ፣ በሙስናና በልዩ ልዩ ክርክር መዛግብት አፈጻጸም፣ በሴቶችና ህጻናት ላይ ከተፈጸሙ ልዩ ልዩ ወንጀሎች አንጻር የማስቀጣት ፍጻሜው በእቅድ ከተያዘው ግብ አንጻር የተሻለ አፈጻጸም የታየባቸው እንደሆኑ ተገልጿል።

በተያያዘም በግማሽ ዓመቱ 33 ሚሊዮን ብር የሚጠጋ በልዩ ልዩ ወንጀሎች የተገኘ ሃብት ለመንግሰት ገቢ እንደተደረገና ህገወጥ የሰዎች ዝውውርን ለመግታታ ከሁሉም ክልሎችና ብሔራዊ ትብብር ጥምረት ጋር በጋራ እየተሰራ እንደሆነ ተገልጿል።

ክሳቸው የተቋረጠላቸው6 ግለሰቦች ክሳቸው እንዲቋረጥ የተደረገበት ምክንያት ላይ ማብራሪያ ቢሰጥ፣ ከህገወጥ የሰዎች፣ የገንዘብና መሳሪያ ዝውውር አንጻር የተሰራው ስራ አጥጋቢ አይደለም፤ በህገወጥ መንገድ ተመዝብሮ በውጪ ባንኮች የተከማቸ ገንዘብን ከማስመለስ አንጻር የተሰራው ስራ ቢገለጽ፤ ከታቀደው ዕቅድ አንጻር አፈጻጸሙ ከፍተኛ ቢሆንም ሕዝብ በፍትህ ስርዓቱ ላይ ያለው እርካታስ ታይቷል ወይ? የሚሉ አስተያየቶችና ጥያቄዎች ከም/ቤቱ አባላት ተነስተዋል።

የፍትህ ሚኒስትሩ ጌዲዮን ጢሞቲዎስ (ዶ/ር) ከጥቅምት 24 የመከላከያ ጥቃት ጋር በተያያዘ በሃገር ህልውናና ህገ መንግስታዊ ስርዓቱን ለመናድ በተፈጸመ ጥቃት ተሳትፎ አላቸው ተብለው ከተያዙ በኋላ በተደረገ ምርመራ የሰውም የሰነድም ማስረጃ ባለመገኘቱ፣ ከግለሰቦቹ ጤና እና ዕድሜ ሁኔታ አንጻር ክሳቸው ቢቋረጥ የህወሐት ቡድን ከሚያሰተላልፈው ፕሮፖጋንዳና የሃሰት ትርክት አንጻር ለሃገር የሚያስገኘውን ጥቅም ከግምት ውስጥ በማስገባት የተወሰነ ውሳኔ

እንደሆነ ክሳቸው የተቋረጣላቸው 6 ግለሰቦች የተፈቱበትን ምክንያት አብራርተዋል።

እክለውም በሃገር ውስጥ የተመዘበረ ገንዘብን ለማስመለስ ከተለያዩ አገራት ልምድ በመውሰድ ባለፉት ሁለት ዓመታት የተጀመረ ስራ በመሆኑና ስራው ጊዜ የሚፈጅ በመሆኑ አፈጻጸሙ ዝቅተኛ እንደሆነ ገልጸው በህገወጥ መንገድ ተመዝብሮ በውጭ ባንኮች የሚገኝ ገንዘብን ለማስመለስ የተደረገው ጥረት ሃገራቱ ገንዘቡ በባንካቸው ቢቆይ ለኢኮኖሚያቸውከሚያስገኘው ጥቅም አንጻር ፈቃደኛ ባለመሆናቸው የተገኘው ውጤት አጥጋቢ እንዳልሆነ አብራርተዋል።

ተቋሙ ካለው ኃላፊነት አንጻር ህገወጥ የሰዎች ዝውውርን ለመግታት ፈጻሚዎችን ወንጀለኛ በማድረግ የሚሰራ ስራ ቢኖርም ከችግሩ ስፋት አንጻር በቂ ስራ እንዳልተሰራ የገለጹት የፍትህ ሚኒስትሩ ፍትህ ርትዕ የሚባሉትን ዕሴቶች በቁጥር ማስቀመጥ ስለማይቻል ከሚቀርቡ እሮሮዎች አንጻር ፍትሕ ተረጋግጧል ማለት እንደማይቻል ገልጸው የሕዝብ እርካታን ለማረጋገጥ ሰፊ ስራ መስራት እንደሚገባ አብራርተዋል።



የህግ፣ ፍትሕና ዴሞክራሲ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ የተከበሩ ወ/ሮ እጸገነት መንግስቱ በሚኒስቴር መ/ቤቱ ዕቅድ አፈጻጸም ላይ ባቀረቡት አስተያየት የአሰራር ስርዓቶች፣ አደረጃጀቶችና የህግ ማዕቀፎች ፍትህ በማስፈን የሕዝብ እርካታን ማምጣት በሚያስችል ሁኔታ መፈተሽ እንዳለበት ገልጸው የፍትህ አካላት ቅንጅት ጉዳይ ፍትሕ ሚኒስቴር የአንበሳውን ድርሻ ሊወስድ እንደሚገባ ገልጸዋል።

# የአገራዊ የምክክር ኮሚሽን ዕጩ ኮሚሽነሮች ዝርዝር ይፋ ተደረገ፤



የኢፌዴሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አገራዊ የምክክር ኮሚሽንን ለማቋቋም የጸደቀውን አዋጅ 1265/2014 ተከትሎ በምክር ቤቱ አፈጉባኤ እና በምክር ቤቱ ጽ/ቤት በተቋቋመ ኮሚቴ አማካኝነት ዕጩ ኮሚሽነሮችን ለመመልመል በርካታ ስራዎችን ሲያከናውን ቆይቷል።

ም/ቤቱ ጥር 27 ቀን 2014 ዓ.ም ከሲቪል ማህበራት ተወካዮች፣ ከሐይማኖት አባቶች፣ ከክልሎች

የአገር ሽማግሌዎች፣ ከወጣት ተወካዮችና የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤቶችን ያሳተፈ ውይይት ለማካሄድ በተዘጋጀው መድረክ ላይ የ42 የኮሚሽኑ እጩ ኮሚሽነሮችን ዝርዝር ይፋ አድርጓል።

ምክር ቤቱ የዕጩ ኮሚሽነሮች ጥቆማ ሕዝብን ያሳተፈ እንዲሆን ለጥቆማ ቅጽ በማዘጋጀት በአካል ወይም በምክር ቤቱ ድህረ ገጽ ከሕዝብ ከተጠቆሙ 632 እጩዎች ውስጥ በዓለም አቀፍም ይሁን የአገር አቀፍ ልምድና ተሞክሮን ታሳቢ በማድረግ 42 እጩ ኮሚሽነሮች እንደተለዩ አብራርተው የ42 ዕጩ ኮሚሽነሮችን ዝርዝር የኢፌዴሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አፈ ጉባኤ ይፋ አድርገዋል።

**“አገርን ወደ አንድ ለማምጣት አገራዊ የምክክር ኮሚሽንን ለማቋቋም የተሄደበት ርቀት የመንግስት አገራዊ ቁርጠኝነትን ያሳያል።”**

መንግስት አገርን ወደ አንድ ለማምጣት አገራዊ የምክክር ኮሚሽንን ለማቋቋም የሄደበት ርቀት ትልቅ አገራዊ ቁርጠኝነት እንደሆነ፣ የተጠቆሙት እጩዎች ወጣቶችንና ሴቶችን ያማከሉ አይደሉም፤ እጩዎች ተመረጡበት አግባብ ግልጽ ቢደረግ፣ የቀረቡት እጩዎች በአብዛኛው የአንድ ፓርቲ አባል በመሆናቸው ገለልተኛ ተቋምን ከመገንባት አንጻር የታየበት ሁኔታ ግልጽ ቢደረግ፣ እጩ ኮሚሽነሮች የኢትዮጵያን ሲቃይ በቃ ብለው በትልቅ አገራዊ አስተሳሰብ መስራት አለባቸው የሚሉ አስተያየቶችና ጥያቄዎችን በውይይቱ የተገኙ ተሳታፊዎች አንስተዋል።





የውይይቱ ሰብሳቢ የተከበሩ አፈጉባኤ አቶ ታገሠ ጫፎ ከውይይቱ ጠቃሚ ግብዓቶች እንደተሰበሰበ፤ እጩዎችን ለመለየትም ብዝሃነትን፣ አቅምን፣ የአገር ውስጥና የውጭ ልምድን ያማከለ እንዲሆን ጥረት እንደተደረገ ገልጸው ሁሉም ባለድርሻ አካላት የሚጠበቅበትን ሚና ከተወጣ በታሪክ አጋጣሚ ለመጀመሪያ ጊዜ አገራዊ ምክክር ለማድረግ የተፈጠረውን እድል ውጤታማ ለማድረግ በቁርጠኝነት መስራት እንደሚገባ አብራርተዋል።

# የሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት የጤና ሚኒስቴርን የ2014 ዓ.ም 6 ወራት እቅድ አፈጻጸም ሪፖርት አዳመጠ፤

የጤና ሚኒስቴር ሚኒስትር ክብርት ዶ/ር ሊያ ታደሰ የጤና ሚኒስቴር ከክልሎች እና አጋር አካላት ጋር በመተባበር ሁለተኛውን የጤና ሴክተር የትራንሰፎርሜሽን የ5 ዓመት እቅድ በማዘጋጀት በጦርነቱ ለወደሙ አካባቢዎች ልዩ እቅድ በማውጣት 42 ሆስፒታሎች፣ 523 ጤና ጣቢያዎች እና 2359 ጤና ኬላዎችን በመንግስት በጀት ብቻ መልሶ መገንባት እንደማይቻል በማመን የሀብት ማሰባሰብ ስራ እየተሰራ መሆኑንና ወደፊትም ተጠናክሮ መቀጠል እንዳለበት አብራርተዋል።



አክለውም የጤና አገልግሎት ጥራትን ከማሳደግ አኳያ እየተገነቡ ከሚገኙ 13 ክልላዊ ላብራቶሪዎች አጠቃላይ ግንባታ በክልሎችና በሁለቱ ከተማ አስተዳደሮች እንዲሁም የኮቪድ 19 እና ተዛማጅ የወረርሽኝ በሽታዎች ህክምና የሚሰጥባቸው የጤና ተቋማት እድሳትና ማስፋፊያ ሥራዎች መሰራቱ በጥሩ ሁኔታ የሚገለጽ ሲሆን፣ የጤና መሰረተ ልማትን ከማሻሻል አኳያ በአዲስ አበባ ከተማ በድንገተኛ ህመም ሊፈጠር የሚችለውን ሞት ለመቀነስ እንዲቻል በከተማዋ በተመረጡ ቦታዎች እየተገነቡ ከሚገኙ ሰምንት የአምቡላንስ ማሰማሪያ ጣቢያዎች አፈፃፀም በጥሩ ሁኔታ ላይ እንደሚገኝ አብራርተዋል።

አሸባሪው ህወሀት ጦርነት ባካሄደባቸው የአማራና አፋር አካበቢዎች ጉዳት የደረሰባቸውን የጤና ተቋማት መልሶ በመገንባት ወደቀደመ አገልግሎታቸው ከመመለስ አንጻርየተሰሩ ሥራዎች ቢኖሩም በሚፈለገው ደረጃ በቂ አለመሆኑ እንዲሁም ጦርነቱ ባልተካሄደባቸው አካባቢዎችም ያሉ የጤና ተቋማት በጦርነቱ ጉዳት የደረሰባቸውን ዜጎች የሕክምና አገልግሎት በመስጠት ላይ ስለነበሩ ተጨማሪ ድጋፍ እንደሚያስፈልጋቸው ከምክር ቤት አባላት ጥያቄና አስተያየት ቀርቧል።

በዚህም መሰረት በአማራ እና አፋር ክልሎች በጦርነቱ ጉዳት የደረሰባቸው እና በጦርነቱ ምክንያት ተጨማሪ አገልግሎት ሲሰጡ የነበሩ የጤና ተቋማትን እንደገና ሥራ ለማስጀመር እና ተጨማሪ ድጋፍ ለማድረግ ከ772 ሚሊዮን ብር በላይ ግምት ያላቸው የመድሐኒት፣ የሕክምና መሣሪያዎች እና የገንዘብ ድጋፍ ከጤና ሚኒስቴርና ከተለያዩ ተቋማት ከፍተኛ ርብርብ በማድረግ የወሊድ አገልግሎትን ጨምሮ ሌሎች መደበኛ አገልግሎቶች

እንዲሰጡ መደረጉን የጤና ሚኒስትሯ አብራርተዋል።

በአጠቃላይ በአማራና በአፋር ክልሎች በአሸባሪው ህወሀት ቡድን የወደሙ 42 ሆስፒታሎች፣ 523 ጤና ጣቢያዎች፣ 2359 የጤና ኬላዎችን መልሶ ለመበገንባት ከ36 ቢሊዮን ብር በላይ እንደሚያስፈልግ ሚኒስትሯ ገልጸዋል።

# የፓርላማ ተመራጭ ሴቶች ኮከስ ምስረታ ተካሄደ፤



የፓርላማ ተመራጭ ሴቶች ኮከስ ከም/ቤቱ ሁለተኛ ዙር ጀምሮ የተቋቋመ ሲሆን አላማውም የሴት የም/ቤት አባላትን አቅም ለመገንባት፣ ተሳታፊነትና ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ፣ ቅንጅታዊ አሰራሮችን ለማጠናከር እና ወሳኝ በሆኑ ጉዳዮች ዙሪያ የአባላትን፣ የአመራሮችንና የተባባሪ ወንድ አባላትን አቅም ለመገንባት የተቋቋመ በም/ቤቱ ካሉ አደረጃጀቶች አንዱ ነው።

ኮከሱ 6ኛውን የኢፌዴሪ የሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት ምስረታን ተከትሎ ባሳለፍነው ጥር ወር የፓርላማ ተመራጭ ሴቶች ኮከስ ምስረታውን በደፋ አካሂዷል።

የሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት ም/አፈጉባኤ የተከበሩ ወ/ሮ ሎሚ በዶ በምስረታ ጉባኤው የመክፈቻ ንግግር ያደረጉ ሲሆን የሴቶችን ሁለንተናዊ ተሳትፎና ተጠቃሚነት የተሟላና ውጤታማ በሆነ መልኩ ለማረጋገጥ ኮከሱ ጠንክሮ መሰራት እንዳለበት ገልጸዋል።

የፓርላማ ተመራጭ ሴቶች ኮከስ አመሰራረቱን በተመለከተ የም/ቤቱ ጽ/ቤት የሴቶች እና ህጻናት ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ወ/ሮ ነጮቴ ፍላቴ ሲያብራሩ ኮከሱ በ1997 ዓ.ም በሁለተኛው ዙር የምክር ቤት ዘመን ተቋቁሞ በሶስተኛው ዙር የምክር ቤት የስራ ዘመን ከ1998-2002 ዓ.ም በማህበራዊ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ በኩል እንደገና ተጠናክሮ ቀጥሏል። ኮከሱ የራሱ ደንብና ስያሜ ወጥቶለት በሰባት ስራ አስፈጻሚ ተዋቅሮ የበላይ ጠባቂ እንዲኖረው ተደርጓል። በተጨማሪም አራት ንዑሳን ኮሚቴዎች በእያንዳንዳቸው አምስት አባላት ያሉት ሲሆን ኮከሱ ሲመሰረት 117 ሴት አባላት እንደነበሩት እና በ5ኛው ም/ቤት 212 ሴቶችና 168 ወንድ ተባባሪ አባላት የነበሩት መሆኑን አብራርተዋል።

የፓርላማ ተመራጭ ሴቶች ኮከስ ከተለያዩ አካላት ጋር በመተባበር የረጅም ጊዜ

ስልጠናዎችን በማዘጋጀት የመጀመሪያ እና የ2ኛ ድግሪ የትምህርት እድል ለኮከሱ አባላት በማመቻቸት የገንዘብ ድጋፍ እንዲያገኙ እና በሶስተኛው የፓርላማ ዘመን ሴቶች ውጭ ሀገር ሄደው የ2ኛ ዲግሪያቸውን እንዲማሩ ያደረገ ሲሆን በተለይም ከሴቶች ህጻናትና ወጣቶች ጉዳይ ሚኒስቴር እና ከሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ ጋር በመተባበር ለሁሉም ክልሎችና የከተማ አስተዳደር ምክር ቤቶች ኮታ በመስጠት ከ3ኛው ዙር የምክር ቤት ዘመን ጀምሮ በየሁለት ዓመቱ ከ120 እስከ 190 ለሚደርሱ ሴቶች የሁለተኛ ዲግሪ የትምህርት ዕድል በማዘጋጀት ሴቶች ብቻ እንዲማሩ ያደረገ መሆኑን አመላክተዋል።

በመጨረሻም ኮከሱን ለቀጣይ አምስት አመታት የሚመሩ አመራሮች የተመረጡ ሲሆን የተከበሩ ወ/ሮ ኪሚያ ጁንዲ የኮከሱ ሰብሳቢ፣ የተከበሩ ወ/ሮ አለሚቱ አበበ ም/ሰብሳቢ እና የተከበሩ ወ/ሮ ቢፍቱ መሀመድ ጸሐፊ አድርጎ በመምረጥ የምስረታ ጉባኤው ተጠናቋል።

# ለበለበ መረጃና አስተያየት

ስልክ ......... 011-1-24-10-65/34
ነፃ ጥሪ........ 8557
መ.ሣ.ቁ........ 80001
ፌስቡክ........... House of Peoples' Representatives of FDRE
ኢ-ሜይል....... parlamainformation@gmail.com

በኢፌዴሪ የሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት ጽ/ቤት
በኮሙኒኬሽን ዳይሬክቶሬት የተዘጋጀ

www.hopr.gov.et